# ጎሕ ቤቶች ባንክ አክሲዮን ማሕበር (በምሥረታ ላይ ያለ)

## ቃለጉባኤ

ሚያዝያ, 2013ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ጎሕ ቤቶች ባንክ አ/ማ የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ

## ቃለ-ጉባዔ

## 1. ጠቅላላ ጉባዔ የተደረገበት ቀን፣ ሰዓትና ቦታ

**1.1.** ስብሰባው የተደረገበት ቦታ፡- አዲስ አባባ ሼራተን **ሆቴል፤**

1.2. ስብሰባው የተደረገበት ቀን፡- መስከረም 28 ቀን 2013 **ዓ/ም፤**

1.3. ስብሰባው የተደረገበት ሰዓት፡- **ከቀኑ 2፡00 እስከ 7፡30 ሰዓት፤**

## 2. የጉባኤው ጥሪ

በፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ እንዲገኙ ለባለአክስዮኖች በንግድ ሕግ ቁጥር 392 እና 395 መሰረት ከጉባዔው ዕለት 15 (አስራ አምስት) ቀኖች አስቀድሞ መስከረም 13 ቀን 2013 ዓ/ም ታትሞ በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ጥሪ ተደረገ።

## 3. የጉባኤውን ጽሕፈት ቤት መቋቋምና በጉባኤው የተገኙ አደራጆችና ታዛቢዎች

### 3.1. የጉባኤውን ጽ/ቤት ማቋቋም

የአደራጅ ኮሚቴው ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ጌታሁን ናና ባለክሲዮኖቹን እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኋላ ወደ ጉባዔው አጀንዳዎች ከመግባቱ በፊት በንግድ ሕግ ቁጥር 404 እና ቁጥር 405 መሰረት የጉባኤው ጽሕፈት ቤት እንዲሰየም ጠየቁ። በዚህም መሰረት፤

3.1.1. የአደራጅ ኮሚቴው ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ጌታሁን ናና ጀንበር የጉባኤው ሰብሳቢ እንዲሆኑ ለጉባኤዔው ሀሳብ ቀረበ፣ ድምጽም ተስጥቶ በሙሉ ድምጽ ጸደቀ።

3.1.2. በንግድ ሕግ ቁጥር 405 መሰረት ሁለት አብላጫ የክሲዮን ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች በድምጽ ቆጣሪነት እንዲሰየሙ የጉባኤው ሰብሳቢ ጠየቁ። በዚህም መሰረት አብላጫና እኩል የክሲዮን ድርሻ ያላቸው ስድስት (6) ባለአክሲዮኖች ተስማምተው ፈቃደኝነታቸውን በማረጋገጥ **ጊፍት ሪል ስቴት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በአቶ ይልማ ተስፋዬ ተወካይ እና አቶ አድማሱ ጤና ወ/የሱስ**



20/05/13

**በአቶ ጌቱ ድንቁ ሥራነህ ተወክለው)** ድምጽ ቆጣሪ እንዲሆኑ ለጉባዔው አቀረቡ፤ ። ጉባዔውም ተቀብሎ በሙሉ ድምጽ አጸደቀ። በመቀጠልም በአደራጅ ኮሚቴው ታጭተው የቀረቡት አቶ መሐሪ ዓለማአየሁ የጉባኤው ጸሃፊ እንዲሆኑ ሰብሰቢው ለጽ/ቤት አባላት ሃሳብ አቀረቡ። የጽ/ቤት አባላትም ሃሳቡን በሙሉ ድምጽ በመቀበላቸው አቶ መሐሪ ዓለማአየሁ የጉባኤው ጸሐፊ ሆነው ተሰየሙ። በመሆኑም ከዚህ በታች በተለመለከተው ሠንጠረዥ 1 የተመለከቱት የጉባዔው ጽ/ቤት አባላት ሆነው በፈራሚዎች ጉባኤ ተሰይመዋል።

ሠንጠረዥ 1፡ የጉባኤው ጽ/ቤት አባላት

| ተ.ቁ | ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታሁን ናና ጀንበር | የጉባዔው ሰብሳቢ |
| 2 | ጊፍት ሪል ስቴት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (በአቶ ይልማ ተስፋዬ ተወክሎ) | ድምፅ ቆጣሪ |
| 3 | አቶ አድማሱ ጠና ወ/የስሱ በአቶ ጌቱ ድንቁ ስራነህ **ተወክለው** | ድምፅ ቆጣሪ |
| 4 | አቶ መሐሪ ዓለምአየሁ | ፀሐፊ |

### 3.2. በጉባኤው ላይ የተገኙ አደራጆች

በሚከተለው ሠንጠረዥ 2 የተመለከቱት የባንኩን ምስረታ ሃስብ ያመነጩ፣ እስካአሁን ያለውን የምስረታ ሂደት በሃላፊነት የመሩ፣ የፈጸሙና ያስተባበሩ እንዲሁም የባንኩን ረቂቅ መመስረቻ ጽሕፍና መተደደሪያ ደንብ በማዘጋጀት በዛሬው ጉባኤ የተገኙ የባንኩ አደራጆች ናቸው።

ሠንጠረዥ 2፡ በጉባኤው ላይ የተገኙ አደራጆች

| ተ.ቁ | ስም | በአደረጅ ኮሚቴው ያላቸው ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታሁን ናና ጀንበር | ሰብሳቢ |
| 2 | አቶ ገ/የሱስ ኢጋታ ሲማ | ምክትል ሰብሳቢ |
| 3 | አቶ ከፈኒ ጉርሙ ገመዳ | አባልና ጸኃፊ |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | ዶ/ር ኢንጂነር ዉብሸት ዠቅአለ መንገሻ | አባል |
| 5 | ዶ/ር ኢንጂነር ሕያው ተረፈ ወ/ዮሐንስ | አባል |
| 6 | አቶ ዮሴፍ አሰፋ ዱባለ | አባል |
| 7 | ወ/ሮ ፋሲካ ከበደ ተመሰለው | አባል |
| 8 | አቶ አርአያ ገ/እግዚአብሔር ገ/ክርስቶስ | አባል |
| 9 | አቶ እሸቱ ፋንታዬ ተሰማ | አባል |
| 10 | አቶ ሙሉጌታ አስማረ በጋለ | አባል |

**3.3.** በጉባኤው ያልተገኙ አደራጅ

አቶ አመርጋ ካሳ ፥ የአደራጅ ኮሚቴ አባል በውጭ ሀገር በመሆናቸው በጉባኤው አልተገኙም።

**3.4. <u>በጉባኤው ላይ የተገኙ ታዛቢዎች፤</u>**

የሚከተሉት ሰዎች ለጉባዔው ታዛቢነት የመጡበትን ተቋም በመወከል ተገኝተዋል።

ሀ. ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

- ወይዘሮ መቅደስ ጨምዴሳ

ለ. ከሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ፤

- አቶ ብዙአየሁ ዓለማየሁ
- አቶ ጥበቡ ካሳሁን

## 4. ምልአተ ጉባኤ

የጉባኤው ሰብሳቢ በንግድ ሕግ ቁጥር 425 መሰረት የዕለቱን የፈራሚዎች ጉባዔ ለማካሄድ የሚያስችል ድምጽ መገኘቱን እንዲያረጋግጡ ድምጽ ቆጣሪዎችን ጠየቁ። ድምጽ ቆጣሪዎችም አስፈላጊውን ማጣራት ከአደረጉ በኋላ የሚከተለውን ሪፖርት ለጉባኤው አቀረቡ።

**4.1.** የመህበሩ ጠቅላላ የተፈረመ የአክስዮን ብዛት 1,143,923 በብር 1,143,923 ,000

**4.2.** የመህበሩ ጠቅላላ የተከፈለ አክስዮን ብዛት **540,264** በብር **540,264 ,000.00**



20/05/13

**4.3.** ድምጽ የማይሰጥባቸው አክስዮኖች ፣ **የሉም፤**

**4.4.** በስብሰባው ላይ የተገኙ አክስዮኖች ብዛት ፤ 591087 በፐርሰንት 52%

**4.5.** በስብሰባው ላይ ያልተገኙ አክስዮኖች ብዛት552,836 በፐርሰንት 48%

**4.6.** ለጉባኤው አስፈላጊ የሆነ አክስዮን ብዛት፤ 571,961 በፐርሰንት 50%፤

ማስተወሻ፣ ስብሰባው ከተጀመረ በኋላ በስብሰባው ላይ የተገኙ አክስዮኖች ብዛት ፤ በፐርሰንት 53 % ሆኗል።

በመሆኑም ድምጽ ቆጣሪዎቹ ከማሕበሩ ባለአክስዮኖች **591087** አክስዮኖችን ወይም 52 % ድምፅ የሚሰጡ አክስዮኖችን የያዙ በመገኘታቸው ፤ በጉባኤው አጀንዳ ላይ በመወያየት ውሳኔ ለማሳለፍ የሚያስችል ምልአተ-ጉባኤ መገኘቱን ለጉባኤው አረጋግጠው ጉባኤው መካሄድ እንደሚችል አሳወቁ። በጉባዔው ላይ የተገኙትን እና ያልተገኙትን ባለአክሲዮኖችና የያዙትን አክሲዮኖች መጠን የሚያመለክት የስም መቆጣጠሪያ (Attendance sheet) ወይም በጉባኤው የመገኘት ማስረጃ ወረቀት ከዚህ ቃለ-ጉባዔ ጋር አባሪ ተደርጎ ተያይዟል ።

## 5. የጉባኤው አጀንዳዎች

በመቀጠልም የጉባኤው ሰብሳቢ በንግድ ህግ ቁጥር 320 መሰረት ተዘጋጅቶ መስከረም 13 ቀን 2013 ዓ/ም ታትሞ በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ለባለክሲዮኖች አስቀድሞ የተገለጹትን የጉባኤውን አጀንዳዎች ለጠቅላላ ጉባኤው እንደሚከተለው በንባብ አሰሙ።

ሀ. የጉባኤውን ጽ/ቤት ማቋቋም

ለ. የአደራጆችን ሪፖርት መስማትና ማጽደቅ

ሐ. የኦዲተሮችን ሪፖርት መስማትና መወሰን

መ. ረቂቅ የመመሥረቻ ጽሑፍ መርምሮ ማፅደቅ

ሠ. የቦርድ አባላትን ሹመት ማጽደቅ

ረ. ረቂቅ የመተዳደሪያ ደንብ መርምሮ ማፅደቅ

ሰ. ኦዲተሮችን መሾምና የአገልግሎት ክፍያቸውን መወሰን

ሸ. ለቦርድ አባላት የሚከፈለውን አበል መወሰን

ቀ. የዕለቱን ቃለ-ጉባኤ ማጽደቅ

## 6. የጉባኤው ውይይትና ውሳኔ

አጀንዳ ሀ፡ የጉባኤውን ጽ/ቤት ማቋቋም

የጉባዔው ጽ/ቤት ከላይ በተራ ቁጥር 3.1 በተመለከተው መሠረት ተቋቁሟል።

አጀንዳ ለ፡ የአደራጆችን ሪፖርት መስማትና ማጽደቅ

_የአደራጅ ኮሚቴውና የዕለቱ ጉባዔ ሰብሳቢ ባንኩን ለመመሥረት እስካሁን የተከናወኑትን አብይ ተግባራት አደራጆችን በመወከል በንባብ ለጉባኤው አሰምተዋል። በሪፖርታቸውም የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች አንስተዋል።

- አደራጅ ኮሚቴው ሃሳብ ከማፍለቅ ጀምሮ ለባንኩ የሚያስፈልገውን ካፒታል እስከ ማሰባሰብ ድረስ ባለፉት ሁለት አመታት ሰፊ ሥራ መስራቱን፥
- የአክሲዮን ሽያጭ ከመጀመሩ በፊት አዳራጅ ኮሚቴው በሀገር ውስጥና በውጭ ባለሙያዎች የአዋጪነት ጥናት ማከናወኑንና በጥናቶቹ ላይ በመመሥረትም በንግድ ሕግ ቁጥር 318 መሠረት መግለጫ (prospectus) ማውጣቱን፥
- አደራጅ ኮሚቴው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን በማስፈቀድ የአክሲዮን ሽያጭ ገቢ የሚደረግባቸውን ዝግ የባንክ ሂሳቦች በአስር ባንኮች መክፈቱንና በማያያዝም በአቶ ጌታሁን ናና እና በአቶ ከፈኒ ጉርሙ የሚንቀሳቀስ የባንክ ሂሳብ በተመሳሳይ ባንኮች የአገልግሎት ክፍያን ለመሰብሰብ መክፈቱን፥
- **በዚህም መሰረት በዝግ ሂሳብ ውስጥ በድምሩ ብር 540.264 ሚሊዮን ከአክስዮን ሽያጭ መሰብሰብ መቻሉን፤**
- **እስከ ሴፕቴምበር 30፣ 2020 ከአክሲዮን ገዢዎች በአገልግሎት ክፍያ መልክ ብር 46. 4 ሚሊዮን መገኘቱን፥**
- **የባንኩ የተፈረመ ካፒታል ብር 1,143,923,000 ቢሊዮን መድረሱን፥**
- አደራጅ ኮሚቴው የባንኩን ምስረታ ሂደት የመራው የፕሮጅክት ጽ/ቤት በማቋቋም እንደሆነና ጽ/ቤቱ አንድ የፕሮጅክት ኃላፊ እንዲሁም ሦስት ሠራተኞች ያሉት መሆኑን፤
- የፕሮጀክቱን ሥራ ለማከናወን እስከ እ.አ.አ. ሴፕቴምበር 30፥ 2020 ድረስ **ብር 8.4 ሚሊዮን** ወጪ እንደተደረገና የወጪው **82% ወይም ብር 6.9 ሚሊዮን** ለማስታወቂያ፥ ለፕሮሞሽንና ለአክስዮን ሽያጭ ወኪሎች ኮሚሽን እንደተከፈለ፥ ቀሪው 18% ለቢሮ ኪራይ፥ ለሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም፥ ለጥናትና የማማከር አገልግሎት፥ ለእዴት አገልግሎት፥ ለህትመት እና ለሌሎች ጥቃቅን ወጪዎች መዋሉን፥ እና

- እነዚህ ወጪዎች ከሞላ ጎደል የተሸፈኑት ከባንክ ወለድ በተገኘ ብር 8.2 ሚሊዮን ገቢ መሆኑንና በዚህም የተነሳ ለእነዚህ ወጪዎች መሸፈኛ ተብሎ ከባለአክሲዮኖች የተሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ እስካሁን የተነካው በትንሹ እንደሆነ፤

ከገለጹ በኋላ በባንኩ ምስረታ ሂደት በሃሳብ፣ በገንዘብና በሞራል ድጋፍ የሠጡትን በሙሉ በኮሚቴውና በራሳቸው ስም በማመስገን ሪፖረታቸውን አጠናቅቀዋል።

ጉባዔው በቀረበው ሪፖርት ላይ አስተያየት እንዲሰጥና ጥየቄ ካለ እንዲያነሳ ተጠይቆ የተለየ አስተያየትም ሆነ ጥያቄ አላነሳም።

በመሆኑም ጉባኤው የሚከተለውን ውሳኔ በሙሉ ድምጽ አሳልፏል።

- የአደራጅ ኮሚቴው ሪፖረት በጉባዔው ተቀባይነት የአገኘ ስለሆነ ጸድቆ። የዚህ ቃለ-ጉበዔ አካል ሆኖ እንዲቀመጥም ተወስኗል።
- ለባንኩ ምስረታ እስከ እ.አ.አ. ሴፕቴምበር 30፣ 2020 ድረስ የወጣው ወጪ በድምሩ ብር **8,369,074.70** ተቀባይነት ያለው በመሆኑ በጉባኤው ጸድቆ የባንኩ ወጪ ሆኖ እንዲመዘገብም ተወስኗል።
- ከአገልግሎት ክፍያ የተሰበሰብውና እስከአሁን ስራ ላይ ያልዋለው ገንዘብ ለባንኩ ወጪዎች መሸፈኛ እንዲውል።

አጀንዳ ሐ፡ የኦዲተሮችን ሪፖርት መስማትና መወሰን፣

ኦዲተሩ ቲ.ኤ.ዋይ የተመሰከረላቸው አዲተሮች መሆናቸውን ተወካዩ አቶ ጉተማ ጀማል አመልክተው የኦዲት ሥነምግባርና መርህ በሚያዘው መሰረት የጎሕ ቤቶች ባንክ አክሲዮን ማህበርን ወጪ መመርመራቸውን ከገለጹ በኋላ በሚከተለው ሠንጠረዥ የተዘረዘሩትን ለጉባዔው በንባብ አሰምተዋል።

20/05/13

ሠንጠረዥ 3፡ የወጪ ዝርዝር

እንደ አሮፓዊያን አቆጣጠር ከኦክቶበር 1፥ 2019 እስከ ሴፕቴምበር 30፥ 2020

| **የወጪው ዓይነት** | **ብር** | **ብር** |
|---|---|---|
| ደመወዝና ጥቅማጥቅም | 98,993.50 | |
| የቢሮ ኪራይ | 122,360.00 | |
| ማስተወቂያና ፕሮሞሽን | 5,045,242.51 | |
| ኮሚሽን | 1,828,239.24 | |
| የሙያና ማማከር አገልግሎት | 826,000.00 | |
| ኦዲት አገልግሎት | 41,400.00 | |
| የመኪናና ትራንስፖርት አገልግሎት | 43,747.00 | |
| የጽህፈት ቤት መሳሪያዎችና አቅርቦቶች | 348,437.45 | |
| ኮሙኒኬሽን አገልግሎት | 14,655.00 | |
| **ድምር** | | **8,369,074.70** |

ኦዲተሮቹ በእነሱ እምነት ከላይ የተዘረዘሩት ሂሳቦች ትክክል መሆናቸውን በመመስከር ሪፖርታቸውን አጠቃልለዋል።

ጉባዔውም የኦዲት ሪፖርቱን አዳምጦ ከተወያየ በኋላ በሙሉ ድምጽ ተቀብሎ አጽድቆታል።

አጀንዳ መ. ረቂቅ የመመሥረቻ ጽሑፉን መርምሮ ማፅደቅ

የጉባኤው ሰብሳቢ በአደራጅ ኮሚቴው ተረቅቆ በቀረበው የማህበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ ላይ ጉባኤው ተወያይቶ አስፈላጊውን ማሻሻያና ማስተካከያ በማድረግ እንዲያጸድቀው ጠየቁ። የሰነዱ ይዘትም አንቀጽ በንአንቀጽ ለጉባዔው ቀረበ። በውይይቱም ወቅት በዋናነት የሚከተሉት ነጥቦች ክርክር ተደርጎባቸል።ይሄውም፥

- በአንቀጽ 7.1 ላይ "የባንኩ አደራጆች ባንኩ ትርፍ ማግኘት ከጀመረበት ሦስተኛ የበጀት ዓመት ጀምሮ ባንኩ አትራፊ ለሆነባቸው ሦስት ዓመታት ከባንኩ የተጣራ ትርፍ ውስጥ 10 (አስር) በመቶ ይከፈላቸዋል" የሚለው ፡ 7% (100 አክሲዮኖችን በያዙ ባለአክሲዮን)፥ 9% (400 አክሲዮኖችን በያዙ ባለአክሲዮን) እና 10% (50000 አክሲዮኖችን በያዙ ባለአክሲዮን) እንዲሆን ሃሳብ ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ድምጽ ተሰጠ። ውጤቱም እንደሚከተለው ሆነ፥
    - ✓ 7% እንዲሆን በሚል የተሰጠ ድምጽ 1,300 አክሲዮኖች (በአራት ባለአክሲዮኖች የተያዘ)፥



NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 10

20/05/13

- ✓ 9% እንዲሆን በሚል የተሰጠ ድምጽ 500 አክሲዮኖች (በሁለት ባለአክሲዮኖች የተያዘ)፣ ሲሆን
- ✓ ድምጸ ተአቅቦ ተጠይቆ፣ የለም
- ✓ 10% በሚል የትሰጠ ድምጽ 589,287

በመሆኑም በስብሰባው ከተገኘው አክሲዮን ጋር ሲነጻጸር ለአደራጆች የሚከፈለው ጥቅም 7% ወይም 9% እንዲሆን የቀረበው ሃሳብ የተደገፈው በድምሩ በ 1,800 አክሲዮኖች ብቻ ሲሆን ለአደራጆች የሚከፈለው ጥቅም 10% እንዲሆን ግን 589,287 በመደግፉ ጉባዔው ከላይ የተጠቀሰው የድምጽ ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ ለአደራጆች የሚከፈለው ጥቅም ከተጣራ ትርፍ ውስጥ 10% እንዲሆን በአብለጫ ድምጽ ፀደቀ።

- በአንቀጽ 7.3 ላይ "የባንኩ መሥራቾች ባንኩ ትርፍ ማግኘት ከጀመረበት ሶስተኛ የበጀት አመት ጅምሮ ባንኩ አትራፊ ለሆነባቸው ሶስት ዓመታት ከባንኩ የተጣራ ትርፍ ውስጥ 6(ስድስት) በመቶ በማህበሩ ውስጥ ባላቸው አክሲዮኖች ድርሻ መጠን ይከፋፈላሉ፡" የሚለው ስምንት ከመቶ (8%) ሆኖ እንዲስተካከል ሃሳብ ቀርቦ በሙሉ ድምጽ ጸደቀ። ይህም ውሳኔ የመመስረቻ ጽሑፍ አካል ሆኖ እንዲመዘገብ ተወስኗል።

በመጨረሻም በተስተካከለው መመሥረቻ ጽሑፍ ላይ ድምጽ ተሰጥቶ ሰነዱ በሙሉ ድምፅ ፀደቀ።

## አጀንዳ ሠ. የቦርድ አባላትን ሹመት ማጽደቅ

የጉባኤው ሰብሳቢ በንግድ ሕግ ቁጥር 350 መሰረት የመጀመሪዎቹ የቦርድ አባላት የሚሰየሙት በመመስረቻ ጽሁፉ መሆኑን በመጥቀስ ስማቸው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት 12 እጩዎች መካከል ዘጠኝ የቦርድ አባላት እንዲመረጡ ጉባዔውን ጠየቁ።

1. አቶ ጌታሁን ናና ጀንበር
2. አቶ ገ/የሱስ ኢጋታ ሲማ
3. አቶ ከፈኒ ጉርሙ ገመዳ
4. ዶ/ር ኢንጂነር ዉብሸት ዝቅአለ መንገሻ
5. ዶ/ር ኢንጂነር ሕያው ተረፈ ወ/ዮሐንስ
6. ወ/ሮ ፋሲካ ከበደ ተመሰለው
7. አቶ አመርጋ ካሳ አምደታ
8. አቶ አርአያ ገ/እግዚአብሔር ገ/ክርስቶስ
9. ወ/ሮ ፅዮን አድማሱ

10. አቶ በላቸው ሁሪሳ

11. ኢትዮ-ላይፍና ጄኔራል ኢንሹራንስ አ.ማ.

12. ሬድዳዋ ሞተርስ ኃ.የተ.የግ.ማ.

የጉባዔው ሰብሳቢ ከላይ በዝርዝሩ የተመለከቱት የተፈጥሮ ሰዎች ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለባንክ ቦርድ አባልነት ያወጣውን መስፍርት የሚያሟሉ እንደሆነ ገለጹ። የሕግ ሰውነት ያላቸው ደግሞ ብቃት ባላቸው ሰዎች እንደሚወከሉም አመለከቱ። በመቀጠልም የአደራጅ ኮሚቴው አባል የሆኑት አቶ ሙሉጌታ አስማረ ዕጩዎቹን አንድ በአንድ ለጉባኤው አስተዋውቁ። ጉባኤውም በየአንዳንዱ ላይ ድምፅ እንዲሰጥ ተደርጎ ውጤቱ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ 4 እንደተመለከተው ሆኗል።

ሠንጠረዥ 4፡ ለቦርድ አባልነት በቀረቡት ላይ የተሰጠ ድምፅ ውጤት

| ተ.ቁ/ደረጃ | ስም | የተሰጠ ድምፅ (በአክሲዮን ብዛት) |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታሁን ናና ጀንበር | 565,284 |
| 2 | ዶ/ር ኢንጂነር ዉብሸት ዝቅአለ መንገሻ | 563,059 |
| 3 | አቶ ገ/የሱስ ኢጋታ ሲማ | 551,953 |
| 4 | ወ/ሮ ፋሲካ ከበደ ተመሰለው | 545,984 |
| 5 | አቶ ከፈኒ ጉርሙ ገመዳ | 514,389 |
| 6 | ወ/ሮ ፅዮን አድማሱ | 502,734 |
| 7 | ኢትዮ-ላይፍና ጄኔራል ኢንሹራንስ አ.ማ. | 494,647 |
| 8 | አቶ በላቸው ሁሪሳ | 480,293 |
| 9 | ሬድዳዋ ሞተርስ ኃ.የተ.የግ.ማ. | 375,283 |
| 10 | አቶ አመርጋ ካሳ አምደታ | 199,786 |
| 11 | አቶ አርአያ ገ/እግዚአብሔር ገ/ክርስቶስ | 163,310 |
| 12 | ዶ/ር ኢንጂነር ሕያው ተረፈ ወ/ዮሐንስ | 135,054 |

በመሆኑም ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ከ 1-9 ከፍተኛ ድምጽ የተሰጣቸው ከታች የተመለከቱት የኅሕ ቤቶች ባንክ አ.ማ. የመጀመሪያው የቦርድ አባላት ሆነው ተሹመዋል።



ናሽናል ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ 10
20/04/13

1. አቶ ጌታሁን ናና ጀንበር
2. ዶ/ር ኢንጂነር ዉብሸት ዠቅአለ መንገሻ
3. አቶ ገ/የሱስ ኢጋታ ሲማ
4. ወ/ሮ ፋሲካ ከበደ ተመስለው
5. አቶ ከፈኒ ጉርሙ ገመዳ
6. ወ/ሮ ፅዮን አድማሱ
7. ኢትዮ-ላይፍና ጄኔራል ኢንሹራንስ አ.ማ.
8. አቶ በላቸው ሁሪሳ
9. ሬድዳዋ ሞተርስ ኃ.የተ.የግ.ማ.

## ረ. ረቂቅ የመተዳደሪያ ደንብ መርምሮ ማፅደቅ

የጉባኤው ሰብሳቢ በአዳራጅ ኮሚቴው ተረቅቆ በቀረበው የማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ጉባኤው ተወያይቶ እንዲያጸድቀው ጠየቁ። የሰነዱ ይዘትም አንቀጽ በንአንቀጽ ለጉባዔው ቀረበ። በዚህም መሰረት፥

- አንቀጽ 6 (ስድስት) "የመክፈያ ጊዜው ካለፈ በኋላ ድርሻውን በወቅቱ ላልከፈለ ባለአክሲዮን ማኅበሩ ክፍያው እንዲደረግ ይጠይቃል። ባለአክሲዮኑ ደብዳቤ በደረሰው 30 ቀን ውስጥ ክፍያውን ባያጠናቅቅ ማኅበሩ ያልተከፈለባቸውን አክሲዮኖች በሀራጅ ለመሸጥ ይችላል" የሚለው 30 ቀኑ 60 ቀን እንዲሆን ተወሰነ።
- የማህበሩን ንብረት የመሸጥ ስልጣን የጠቅላላ ጉባኤው ቢሆን የሚል ሃሳብ ቀርቦ ከአሰራርም ሆነ ከህግ አንጻር ታይቶ በረቂቁ በቀረበው መሰረት እንዲሆን ተወስኗል፥
- እንደ አስፈላጊነቱ የንግድ ህግ ቁጥሮች በመተዳዳሪያ ደንቡ እንደማጠቀሻ ይግቡ የሚለው ሃሰብ ቀርቦ ይሁንታ ስለአገኘ ቦርዱ ሃላፊነት ወስዶ እንደአስፈላጊነቱ አስፈላጊ የሆኑ የንግድ ህግ ቁጥሮች በመተደደሪያ ደንቡ እንዲያስገባ ተወስኗል።

በመጨረሻም በተስተካከለው የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ድምጽ ተሰጥቶ ሰነዱ በሙሉ ድምፅ ፀደቀ።

## አጀንዳ ሰ. ኦዲተሮችን መሾምና የአገልግሎት ክፍያቸውን መወሰን

የጉባኤው ሰብሳቢ በንግድ ሕግ ቁጥር 369 መሰረት የመጀመሪያውን የባንኩን የሂሳብ አመት የሥራ ክንውን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር ጉባኤው እንዲሾም ጠየቁ። በማስቀጠልም አቶ ሙሉጌታ አስማረ የኦዲተሮችን መረጣ ሂደት

እንዲያብራሩ ሰብሳቢው ጠየቁ። አቶ ሙሉጌታም ለሹመቱ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት አደራጅ ኮሚቴው ለሰስት ኦዲተሮች የግብዣ ደብዳቤ ልኮ ሁለቱ መልስ ሲሰጡ አንዱ መልስ አልሰጠም። መልስ ከሰጡት ኦዲተሮች መካከል የቴክኒክና የፋይናንስ ግምገማ ተደርጎ በቴክኒክ ከፍተኛ ውጤት አምጥቶ በዋጋ ዝቅተኛ የሆነው ቲ.ኤ.ዋይ የተመሰከረላቸው ኦዲተሮች የባንኩ የመጀመሪየው አመት ኦዲተሮች እንዲሆኑና ለመጀመሪያው ሂሳብ አመት ኦዲት አገልግሎት ብር 96,600 እንዲከፈላቸው ሃሳብ አቀረቡ።

ጉባኤውም በጉዳዩ ላይ ተወያይቶ አደራጅ ኮሚቴው ባአቀረበው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት ቲ.ኤ.ዋይ የመጀመሪያው የሂሳብ ዓመት የባንኩ ኦዲተር እንዲሆንና በንግድ ህግ ቁጥር 372 መሠረት ለአገልግሎቱም ብር 96,600 እንዲከፈለው በሙሉ ድምፅ ወስኗል።

አጀንዳ ሸ፡ ለቦርድ አባላት የሚከፈል አበልን መወሰን

የጉባዔው ሰብሳቢ በንግድ ህጉ ቀጥር 353 እንደተደነገገው ጉባዔው ለቦርድ አባላት መከፈል ያለበትን አበል መወሰን እንደሚኖርበትና ከዚህ ጋር ተያይዞም በኢትዮጵ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ለቦርድ አባላት የሚከፈለው አመታዊና ወርሃዊ ክፍያ እንደቀደም ተከተላቸው ከብር 150000 እና ከብር 10000 መብለጥ እንደማይችል ገለጹ። ጉባዔውም በጉዳዩ ከተወያየ በኋላ የቦርድ አባላት ወርሃዊ ክፍያ ብር 10000 (ከታክስ በኋለ) እንዲሆን አመታዊ ክፍያ ደግሞ ብር 150 000(ከታክስ በኋላ) እንዲሆን በሙሉ ድምፅ ወሰነ።

አጀንዳ ቀ፡ የዕለቱን ቃለ-ጉባኤ ማጽደቅ

በመጨረሻም የጉባኤው ሰብሳቢ የዕለቱን የጉባዔውን ቃለጉባዔ የጉባዔው ፀኃፊ በንባብ እንዲያሰሙ ጠየቁ። የጉባዔው ፀኃፊም ቃለ-ጉበዔውን በንባብ አሰሙ። ጉባዔውም ቃለ-ጉባዔውን በሙሉ ድምጽ አጸደቀው። የዕለቱ ስብሰባም ከቀኑ 7:30 አበቃ።

7. ማረጋገጫ

ሀ. እኛ የጎህ ቤቶች ባንክ አ/ማ የጽ/ቤት አባላት የጎሕ ቤቶች ባንክ አ.ማ. የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባኤ በመስከረም 28 ቀን 2013ዓ.ም በሼራተን አዲስ አባባ ሆቴል መካሄዱን፣ በጉባኤው ላይ የመገኘት ማስረጃ ወረቀቱ ወይም የስም መቆጣጠሪያው ትክክለኛ መሆኑን እና የጉባኤው የውይይት ውሳኔዎች በትክክል በቃለ ጉባኤው ላይ መስፈራቸውን በንግድ ሕግ ቁጥር 403 (2) መሰረት እናረጋግጣለን።

Authentication and Registration Agency Addis Ababa (Branch Ten Office)

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

20/05/13

| ተ.ቁ | ስም | ኃላፊነት | ስምና ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታሁን ናና ጀንበር | ሰብሳቢ | |
| 2 | ጊፍት ሪል ስቴት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (በአቶ ይልማ ተስፋዬ ተወክሎ) | ድምፅ ቆጣሪ | |
| 3 | አቶ አድማሱ ጠና( በአቶ ጌቱ ድንቁ ስራነህ ወኪልነት ) | ድምፅ ቆጣሪ | |
| 4 | አቶ መሐሪ ዓለምአየሁ | ፀሐፊ | |

ለ. እኛ በኅሕ ቤቶች ባንክ አ/ማ የተገኘን አደራጆች የኅሕ ቤቶች ባንክ የፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባኤ መስከረም 28 ቀን 2013 ዓ.ም መካሄዱን፣ ተዘጋጅቶ የቀረበው በጉባኤው ላይ የመገኘት ማስረጃ ወረቀት ወይም የስም መቆጣጠሪየው ትክክለኛ መሆኑን፣የዕለቱ ጉባኤ በዚህ ቃለ ጉባኤ የተገለፁትን ውሳኔዎች ማሳለፉን እና የጉባኤው ውይይት ውሳኔዎች በትክክል በቃለ ጉባኤው ላይ የሰፈሩ መሆናቸውን እናረጋግጣለን።

| ተ.ቁ | ስም | በአደረጅ ኮሚቴው ያላቸው ኃላፊነት | ስምና ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታሁን ናና ጀንበር | ሰብሳቢ | |
| 2 | አቶ ገ/የሱስ ኢጋታ ሲማ | ምክትል ሰብሳቢ | |
| 3 | አቶ ከፈኒ ጉርሙ ገመዳ | አባልና ጸኃፊ | |
| 4 | ዶ/ር ኢንጂነር ዉብሸት ዝቅአለ መንገሻ | አባል | |
| 5 | ዶ/ር ኢንጂነር ሕያው ተረፈ ወ/ዮሐንስ | አባል | |
| 6 | አቶ ዮሴፍ አሰፋ ዱባለ | አባል | |
| 7 | ወ/ሮ ፋሲካ ከበደ ተሰማ | አባል | |
| 8 | አቶ አርአያ ገ/እግዚአብሔር ገ/ክርስቶስ | አባል | |

Authentication and Registration Agency Addis Ababa Branch Ten Office



የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 10

| | | | |
|---|---|---|---|
| 9 | አቶ እሸቱ ፋንታዬ ተሰማ | አባል | |
| 10 | አቶ ሙሉጌታ አስማረ ቦጋለ | አባል | |

የአስፈራሚው ስም_______________________________________

ፊርማ_______________________________________________

ለጉባኤው የቀረቡ ሰነዶች

1. የአደራጆች ሪፖርት
2. የኦዲተሮች ሪፖርት
3. መመሥረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ